1.ሪፖርት ላኪ፡- የዳውሮ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ

2. ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ፡- ከሐምሌ 01/2001 -መስከረም 30/ 2002

3. የታቀዱ ተግባራትና ዝርዝር ክንውን

**3.1. በዞኑ በሚገኙ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደር የመንግስት ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በተሟላ ሁኔታ የተተገበረ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ፡-**

- በዞኑ በሚገኙ በ1ኛው ዙር ወደመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ የገቡ 7 ሴክተር መ/ቤቶች ባሳለፍነው ሩብ ዓመት በየሳምንቱ የድጋፍና ክትትል እየተደረገላቸው ሲሆን የመምሪያችን የለውጥ ፐሮ/ፐሮ/ጥናትና ትግበራ ዋና የሥራ ሂደት በአፈጻጸም ሰነዱ ውል ሰነድ መሰረት በየጊዜው ግብረመልስ እየሰጠ የሚሰራበት ሁኔታ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡በተጨማሪም ተቋማት እመርታዊ ለውጥ እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ በየሥራ ሂደቶቹ ክትትልና ድጋፍ ተደርጎ ግብረ-መልስ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- በ2ኛው ዙር ወደ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ የሚገቡ ሴክተሮች በሰው ኃይል፤ በመስሪያ ቦታና ቢሮ አደረጃጀት፣ በበጀትና ሎጅስቲክ ያደረጓቸውን ቅድመ-ዝግጅቶች በመከታተል የማብቃት ሥራ ከመሰራቱም በላይ ሠራተኞቻቸውን በህሊና ዝግጅት ረገድ እንዲያዘጋጇቸው አዋጅ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡
- በተጨማሪም ከመስከረም 21/2002 ጀምሮ የ2ኛው ዙር መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ የተጀመረ ሲሆን የሰው ኃይል ምደባ መረጃ (የተመደቡ፤ያልተመደቡ፣በባለሙያ የተያዙና ያልተያዙ የሥራ ሂደቶች) ዝርዝር እየተሰባሰበ ይገኛል፡፡

**3.2. በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሠራር**

- ባሳለፍነው ሩብ ዓመት በመጀመሪያ ዙር ትግበራ በገቡ ሴክተሮች የተገልጋ ቅሬታ ማስተናገጃ እርካታ መግለጫ ፎርማቶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ከመዋላቸውም በላይ ተገልጋዮች በተቻለ መጠን አስተያየትና ቅሬታ የመግለጽ ልምድ እንዲኖራቸው ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

- የአስተያየት መስጫ መዝገቦችና ሣጥኖች ህብረተሰቡ በሚያዘወትሯቸው ሥፍራዎች በማስቀመጥ ስለአገልግሎታቸው የህብ/ሰቡን አስተያየት የሚሰበስቡ እንደፖሊስ መምሪያ ያሉ ተቋማት ልምዳቸውን በማስፋት ለሌሎች የማካፈል ተግባር እንዲለመድ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

**3.3. በዞኑ በሁሉም ወረዳና ከተማ አስ/ር የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ትግበራ**

- በዞኑ በሚገኙ 172 ቀበሌያት የመልካም አስ/ር ፓኬጅ ትግበራ የሚደግፉ የሥራ አስኪያጆች የተመደቡ ሲሆን ባሳለፍነው ሩብ ዓመት በማረቃ ከሥራ በለቀቁት 10 የሥራ አስኪያጆች ከተተኩት በስተቀር ሁሉም ሥልጠና ያገኙና የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ናቸው፡፡
- በሁሉም ቀበሌያት የተገልጋይ አስተያየት መስጫ መዝገብና የአቤቱታ ማቅረቢያ ፎርም ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን በቀበሌው ከሚገኙ ነዑሳን ኮሚቴዎች ጋር በመሆን የትግበራ ዕቅድ በማዘጋጀት ኃላፊነትን በወልና በተናጠል እየተወጡ ሲሆን በሁሉም የልማት ተግባሮቻችን ላይ ቅድሚያ የህብረተሰቡን አመኔታ የሚያገኙበት አሰራር ተዘርግቷል፡፡
- በሁሉም ቀበሌዎች የማስፋት ተግባራትን ለመደገፍና አርሶ አደሩ ከግብዓት ጀምሮ በሁሉም ተግባራቱ በዕቅድ የሚመራበት እንቅስቃሴ የታየ ሲሆን በቀበሌው ውስጥ በሚገኙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ተግባራዊ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡
- በሁሉም ቀበሌዎች ህብረተሰቡን አሳምኖ ወደተሳትፎ የማስገባቱ ሥራም በተጠናከረ መልኩ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

**3.4. በሁሉም የፍትህ ተቋማት የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበር ተደራሽ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል**

- በሁሉም የፍትህ ተቋማት በተጠናው የመሰራታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ መሰረት ተጣቃለው ወደትግበራ የገቡበት አሰራር የተዘረጋ ሲሆን የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶችን ተተካክቶ በመሥራት/ወንጀል መከላከልየሥራሂደት ሃላፊነትን በመወጣት ይገኛሉ፡፡ የፍትህ ተቋማቱ በየጊዜው በሚሰጣቸው ድጋፍና ክትትል እየታገዙ አማካይ በሆኑና አመቺ ሥፍራዎች ተዘዋዋሪ ችሎቶችን በመዘርጋት ተገልጋዩን ህብረተሰብ በቅርበት በማገልገል ላይ ይገኛሉ ፡፡

- ሁሉም የፍትህ ተቋማት ፍትህን ፈጣን፤ተደራሽና ቀልጣፋ ከማድረግ አኳያ አስፈላጊው ሁሉ ርብርብ እየተደረገ ሲሆን፤የዞኑ ፍትህ ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴና የቴክኒክ ኮሚቴ የዘመኑን የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራሞች ለመምራትና ከተፈላጊው ግብ ለመድረስ ይቻል ዘንድ ያለፈውን ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም የ2002 ዓ.ም ዕቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ከመገኘቱም በላይ የ1ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ አድርጓል፡፡ በወቅቱም በውሳኔ አሰጣጥ ግልጸኝነት መጓደል፣በማስረጃ አቀራረብ ግድፈት ዙሪያ፣ በወንጀል መከላከልና ከማረሚያ በምህረት የሚለቀቁ ታራሚዎች የሚፈጽሟቸው ወንጀሎችና ህብረተሰቡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች እንዲሁም መሬት ይዞታ ክርክር በየወቅቱ እየተከታተሉ የማረምና አስፈላጊውን ድጋፍ የመስጠት ተግባር ለማድረግ አስተባባሪና የቴክኒክ ኮሚቴው በዋናነት ተወያይቶ ውሳኔ አስተላለፏል፡፡
- በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ በወንጀል መከላከል የሥራ ሂደት የተመደቡ የፖሊስ አባላት ከህብረተሰቡ ጋር በመተባበር እስከቀበሌ ወርዶ በመስራትና በዞኑ ባሉት 172 ቀበሌያት የኮሙኒቲ ፖሊሲንግ ሥርዓት ዘርግቶ ህብረተሰቡን ያሳተፈ የመከላከል ተግባር እየተከናወነ ይገኛል፡፡
- በፍርድ ቤቶች ማሻሻያ የአቤቱታ መስማትና መወሰን የስራ ሂደት ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት ይቻል ዘንድ በሙሉ ኃይሉ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን በተለይም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግድግዳዎችን በማፍረስ በአዲስ የቢሮ አደረጃጀት ለተገልጋይ ምቹ መስተንግዶ የሚሰጥበት አሰራር አመቻችቷል፡፡
- የማረሚያ ተቋማችንም የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በተሻለ ሁኔታ የሚጎለብቱበትን አቅጣጫ እንዲይዙ ለማድረግና ታራሚዎች በቆይታቸው ወቅት በክህሎት የሚታነፁበት እንዲሆን ለማመቻቸት በብረት ሥራ ፤በእንጨት ሥራና በሽመና የባለሙያ ቅጥር ለማከናወን እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ነው፡፡

### 3.5. በዞኑ የተዘረጋ ፣የተስፋፋና ሥራ ላይ የዋለ የኢኮቴ መሰረተ ልማት

- መምሪያው በተጠቀሰው ዘርፍ የነበረበትን የባለሙያ ዕጥረት ለመቅረፍ የ1 ባለሙያ ቅጥር ያከናወነ ሲሆን በማህበረሰብ የመረጃ ማዕከልም መሠረታዊ የኢንተርኔት አጠቃቀም ሥልጠና ለመስጠት ዝግጅቶች እየተደረጉ ይገኛል፡፡

- የዳውሮ ልማት ማህበር ያስመጣቸውን ኮምፒውተሮች ለሚገዙ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት 80 ኮምፒወተሮች ሽያጭ ተከናውኗል፡፡
- ባሳለፍነው ሩብ ዓመት የ3 ፎቶ ኮፒ፤1ፋክስና 1 ፐሪንተር በብር 1240.00 ጥገና ተከናውኗል፡፡
- ወደ ሙሉ አገልግሎት ሊገቡ የሚገባቸው የቪዲዮ ኮንፍረንሲንግ መሣሪያዎች አገልገሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ሁኔታዎችን የማመቻቸትና ከክልሉ ዋና የሥራ ሂደት ጋር ግንኙነት የመፍጠር ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው፡፡

3.6. በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግስት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ

- በሰው ሃብት ሥራ አመራር ዋና የሥራ ሂደት በዞኑ የሚገኙ ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ በሰው ኃይል የተደራጀ ሲሆን በቅርቡ ወደ ትግበራ የገቡ ሴክተሮችን መረጃ የማሰባሰብና ለዳታ ኢንኮዲንግ የማመቻቸት ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

3.7. የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈጻጸም ችግሮች ቅሬታዎችና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች

- ባለፈው ሩብ ዓመት መመሪያና ደንብን በጥልቀት ካለመገንዘብና ብሎም ከቅንነት ማጣት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ የአፈጻጸም ችግሮችን ከሥሩ ለማድረቅ ባለሙያው መመሪያና ደንብ እንዲደርሰው በማድረግ፤
- ችግሮችም ሲፈጠሩ ምንጫቸው ድረስ በመሄድ መረጃ በመሰብሰብና በማጣራት እርምት እንዲደረግባቸው የዘወትር ጥረት እየተደረገ ከመሆኑም በላይ በወጣቶችና ስፖርት መምሪያ የኦፊስ አሲስታንስ አወዛጋቢ ቅጥር፤በተርጫ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የተፈጠረው ከተፈላጊ ችሎታ ውጭ በዘፈቀደ የተሰጠ ምደባ ግድፈት፤በዞኑ ማረሚያ ተቋም መመሪያና ደንብን ባልተከተለ ሁኔታ የተከናወነ የሾፌር ኮንትራት ቅጥር እንዲታረሙ አቅጣጫ የተቀመጠ ሲሆን፤ በማረቃ ወረዳ ፍትህና ፀ/ጽ/ቤት በመርማሪ ከሳሽነት ምደባ የተሰጣቸው ባለሙያ እስካሁን ሥራ እንዳይጀምሩ የተደረገበት ሁኔታ ማጣሪያ እንዲደረግበት ቡድን ተልኳል፡፡

4. ያጋጠሙ ችግሮች

- በ2ኛው ዙር ወደ መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ የሚገቡ ሴክተሮች ለሁሉም ሥልጠና አለመሰጠትና የአፈጻጸም መመሪያዎች አለማግኘት፤

- ሴክተሮች የሚፈልጉትን የሰው ኃይል በተፈላጊ ችሎታና በሥራ ሂደት ለይቶ ያለማሳወቅ ፤
- የኢኮቴ መሳሪያዎች በተፈላጊው መጠን ተሟልተው ያለመኖር፤
- በየሥራ ሂደቶቹ ዘግይተው የተመደቡ ባለሙያዎች ሥልጠና ያለማግኘት ፤
- የወረዳ ኢንስፔክሽን ቡድን አደረጃጀትና አሠራር መመሪያ መዘግየት፤
- የማህበረሰብ የመረጃ ማዕከል ተፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት ይችል ዘንድ መመሪያና ደንብ ያለመኖር፣ፕሪንተርና ፎቶኮፒ ማሽን ተሟልቶ ያለመገኘት፤
- በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ የተቃኘ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ ዝግጅት ሥልጠና ያለመሰጠት ።

5. የተወሰዱ መፍትሔ አቅጣጫዎች

    - ሴክተሮች የተሟላ የሰው ኃይል እንዲያገኙ ፍትሃዊ የሰው ኃይል ድልድል ተከናውኗል።
    - ባሉት የኢኮቴ መሣሪያዎች የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ ለማድረግ እየተሞከረ ነው።
    - በ2ኛው ዙር መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ሙሉ ትግበራ ለገቡ ለሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች ሥልጠና እንዲሰጥ ከክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ለድጋፍና ክትትል ለተሰማሩ ባለሙያዎች ማስታወሻ እንዲይዙ ተደርጓል።
    - የማህበረሰብ መረጃ ማዕከል በደንብና መመሪያ እንዲመራ እንዲሁም ፎቶኮፒና ፕሪንተር እንዲሰጠን ለክልል አቅም ግንባታ ቢሮ ለኢኮቴ መሰረተ-ልማትና አቅርቦት ዋና የሥራ ሂደት ጥያቄ ቀርቧል።